AMHARIC

# የዩናይትድ ስቴትስ ካፒቶል
# ጎብኚዎች መመሪያ



U.S. CAPITOL
የጉብኝት ማዕከል



# ወደ ዩኤስ ካፒቶል እንኳን በደህና መጡ

ታሪካዊው የዩኤስ ካፒቶል ጉብኝትዎ የሚጀምረው ወደ ካፒቶል የጎብኚዎች ማዕከል ሲገቡ ነው። የካፒቶል ጎብኚዎች ማዕከል እጅግ የዘለገ ቁመት ባለው ጉልላቱና ብርሃን በሚያሳልፈው ጣሪያው አዲስ ዕውቀት ወደ ሚሸምቱበት ጉብኝት ይቀበልዎታል። የዩኤስ ካፒቶል የዩኤስ ኮንግረስና የሁለቱ ሕግ አውጪ አካል የሆኑት የዩኤስ የእንደራሴዎች ምክር ቤትና የዩኤስ ሴኔት መቀመጫ ነው። በፊልሞች፣ በአውደ ርዕዮችና በጉብኝት ኮንግረስ እንዴት እንደሚሰራ፣ ታላቁ ሕንጻው እንዴት እንደተገነባና ዜጎች የውክልና ዴሞክራሲ በመባል በሚታወቀው ከፍ ያለ ትርጉም ባለው ሂደት እንዴት እንደሚሳተፉ ትምህርት ይቀስማሉ።



ዘ አፖቴዮሲስ ኦፍ ጆርጅ ዋሽንግተን

የዩኤስ ካፒቶል እንደ የአሜሪካ ህዝብ ሃውልት ሆኖ ቆሟል። በዚህ ሥፍራ አገሪቱን የሚያጋጥሟት ጉዳዮች ይታያሉ፣ ክርክር ከተደረገባቸው በኋላ ሕግ ሆነው ይጸፋሉ። ከዚህም ሌላ በዩኤስ ካፒቶል የታወቁ የአሜሪካ ስዕሎች ስብስብ ይገኛል፤ ሕንጻውም በራሱ ታላቅ የኪነ ሕንጻ ስኬት ነው። በዩኤስ ካፒቶል ታሪክ ይሰራል፤ የካፒቶል የጎብኚዎች ማዕከል ደግሞ ወደዚያ ታሪክ የሚገቡበት በር ነው።

በዲሴምበር 18 ቀን 2007 የዩኤስ ካፒቶልን ለገነቡ ባሮች የጉልበት ሠራተኞች እውቅና ለመስጠት ኮንግረስ የካፒቶል ጎብኚዎች ማዕከል ማዕከላዊ ቦታ "ኢማንሲፔሽን አዳራሽ" ተብሎ እንዲጠራ በሕግ አወጀ። በካፒቶል ጎብኚዎች ማዕከል የታችኛው ደርብ የሚገኘው ኢማንሲፔሽን አዳራሽ ካፒቶልን ለማየት ወደ ካፒቶል የሚመጡ ጎብኚዎች የሚሰበሰቡበት ሥፍራ ነው።

## ዩኤስ ካፒቶልን በአስጎብኚዎች እገዛ ስለመጎብኘት

በአስጎብኚዎች በመታገዝ የሚካሄደው የካፒቶል ታሪካዊ ጉብኝት የሚጀምረው በካፒቶል የጎብኚዎች ማዕከል የታችኛው ደርብ በሚገኙ የማስተዋወቂያ አዳራሾች ነው። የ13 ደቂቃ ርዝመት ያለው "Out of Many, One" የተሰኘ ፊልም ይህች አገር እንዴት አዲስ ዓይነት መንግሥት እንደመሰረተች፣ ኮንግረስ በአሜሪካዊያን የዕለት ተዕለት ሕይወት ውስጥ የሚጫወተውን ሚና ከማብራራቱ በተጨማሪ የዩኤስ ኮንግረስ ስለሚገኝበት ሕንጻ ለጎብኚዎች መረጃ ይሰጣል።



ጉብኝቶች ከክፍያ ነጻ ሲሆኑ፤ ዘወትር ከሰኞ እስከ ቅዳሜ ከ8፡40 a.m. እስከ 3፡20 p.m. ያካሄዳሉ። ለመጎብኘት የጉብኝት የይለፍ ፈቃዶች ያስፈልጋሉ።

**ቅድሚያ የይለፍ ፈቃዶች፡-** ጉብኝቶች በwww.visitthecapitol.gov ወይም ከመጡበት ግዛት ሴኔተሮች ወይም ተወካዮች ቢሮዎች ወይም በስልክ ቁጥር 202.226.8000 በመደወል አስቀድሞ ወረፋ ሊያዝላቸው ይቻላል።

**በእለቱ የሚሰጡ የይለፍ ፈቃዶች፡-** በጎብኚዎች ማዕከል የታችኛው ደርብ በሚገኘው የኢማንሲፔሽን አዳራሽ የመረጃ ዴስኮች የተወሰኑ የይለፍ ፈቃዶች ይገኛሉ።

## ልዩ ጉብኝቶችና ፕሮግራሞች

ስለ ኮንግረስና ካፒቶል ታሪክ በልዩ ጉብኝትና ተግባራት አማካኝነት ይበልጥ ይማሩ። በኢሚኒሴፔሽን አዳራሽ ባሉ የመረጃ ዴስኮች ወይም በwww.visitthecapitol.gov አማካኝነት ወቅታዊ የሆኑ የጊዜ ሰሌዳዎች መረጃ ያግኙ።

## የትዕይንት አዳራሽ (የታችኛው ደርብ)

በአገሪቱ ስለ ኮንግረስና ስለ ዩኤስ ካፒቶል ግንባታ ታሪክ ለመንገር ብቻ የተዘጋጀውን ብቸኛ ትዕይንት ይታደሙ። የትዕይንቱ ዋና ዋና ክፍሎች ከብሔራዊ የሰነድ ማስቀመጫና ከላይብራሪ ኦፍ ኮንግረስ የተገኙ ታሪካዊ ቁሶችን ያካተተ ነው፤ በተጨማሪ 11 ጫማ ቁመት ያለው በእጅ ሊነካ የሚችል የካፒቶል ጉልላት ናሙና ይገኛል። ኮንግረስ በስብሰባ ላይ በሚሆን ጊዜ የእንደራሴዎች ምክር ቤትና የሴኔት ስብሰባዎችን በምክር ቤቶቹ ቲያትሮች መመልከት ይችላሉ። መልስ መስጫ ጣቢያዎች ስለኮንግረስ፣ ስለአባላቱና ስለካፒቶል ተጨማሪ መረጃ እንዲያገኙ ከሰኞ እስከ ቅዳሜ ከ8:30 a.m. እስከ 4:30 p.m. እገዛ ይሰጣሉ።



## ኮንግረስን በስብሰባ ላይ እያለ ስለመመልከት

**የይለፍ ፈቃዶች፡-** የሴኔትና የሕዝብ እንደራሴ ምክር ቤት ጋለሪዎች የሴኔት ወይም የህዝብ እንደራሴዎች ምክር ቤት በስብሰባ ላይ በሚሆኑ ጊዜ ለሕዝብ ክፍት ናቸው፤ ሆኖም ግን ጋለሪዎቹ በዩኤስ ካፒቶል ጉብኝት ውስጥ አይካተቱም። የይለፍ ፈቃዶች የሚያስፈልጉ ሲሆኑ እነርሱንም ከመጡበት ግዛት ሴኔተሮች ወይም እንደራሴዎች ቢሮ ማግኘት ይችላሉ። ወደ ጋለሪዎቹ የሚያስገባው የመጀመሪያ ስፍራ የካፒቶል የጎብኚዎች ማዕከል የላይኛው ደርብ ነው። ዓለም ዓቀፍ ጎብኚዎች በላይኛው ደርብ በሚገኘው የእንደራሴዎችና የሴኔት የቀጥር ዴስኮች ጥያቄ ማቅረብ ይችላሉ።





**የሕዝብ እንደራሴዎች የሥራ ሰዓታት፡-** የሕዝብ እንደራሴዎች ምክር ቤት በስብሰባ ላይ በማይሆንባቸው ጊዜያት የይለፍ ፈቃድ የያዙ ጎብኚዎች ወደ ጋለሪው ከ9 a.m. እስከ 4 p.m. ከሰኞ እስከ ዓርብ መግባት ይችላሉ። የእንደራሴዎች ምክር ቤት በስብሰባ ላይ ካልሆነ በስተቀር ጋለሪው በሳምንት የዕረፍት ቀናትና በበዓላት ቀናት ዝግ ነው። ምክር ቤት ስብሰባ ከሌለው የምክር ቤቱ ጋለሪ ባልታቀደ ሁኔታና በጊዜያዊነት ሊዘጋ ይችላል። ስለ ሕዝብ እንደራሴዎች ምክር ቤት ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት www.house.gov ን ይጎብኙ።

**የሴኔት የሥራ ሰዓታት፡-** የሴኔት ጋለሪ ለአንድ ሣምንት ወይም ከዚያ በላይ ለሆነ ጊዜ በሚኖረው ዕረፍት ወቅት ክፍት ነው፤ የይለፍ ፈቃድ ያያዙ ጎብኚዎች ከ9 a.m. እስከ 4:15 p.m. ከሰኞ እስከ ዓርብ መጎብኘት ይችላሉ። ሴኔቱ በስብሰባ ላይ ካልሆነ በቀር በሣምንት የዕረፍት ቀናትና በበዓላት ቀናት እንዲሁም በማናቸውም ከአንድ ሣምንት በታች ለሆነ የዕረፍት ጊዜ ወይም ሴኔት ስራውን ሲያቋርጥ ጋለሪው ዝግ ይሆናል። መረጃ ለማግኘት እባክዎን በስልክ ቁጥር 202.224.0057 ይደውሉ።

## ላይብራሪ ኦፍ ኮንግረስ

ጎብኚዎች ከካፒቶል የጎብኚዎች ማዕከል በአገሪቱ ታላላቅ ሀብቶች መካከል አንዱ ወደሆነው ታሪካዊው የቶማስ ጀፈርሰን የላይብራሪ ኦፍ ኮንግረስ ሕንጻ በላይብራሪ ኦፍ ኮንግረስ መተላለፊያ ዋሻ በኩል በቀጥታ ለመግባት ፈቃድ ያገኛሉ። የመተላለፊያው ዋሻ መግቢያ በካፒቶል የጎብኚዎች ማዕከል የላይኛው ደርብ በእንደራሴዎች ምክር ቤት የቀጠሮ ዴስክ አቅራቢያ ይገኛል።



## የካፒቶል ዙሪያ ገብ

ካፒቶል በ58.8 ኤከር ያረፈ፣ ጠመዝማዛ መንገዶች፣ መታሰቢያ ዛፎች፣ መስብህነት ያላቸው መቀመጫዎችና በየወቅቱ የሚቀያየሩ ማራኪ አበቦች ያሉት ነው። የካፒቶል ዙሪያ ገብ የአትልክት ሥፍራ በታዋቂው ባለሙያ ፍሬድሪክ ሎው ኦልምስቴድ በ1892 የተነደፈ እቅድን የተከተለ ነው። በካፒቶል ዙሪያ ገብ ውስጥ ሲዘዋወሩ፣ በኢስት ፕላዛ እጅግ ያማሩ በነሃስና በድንጋይ የተሰሩ ፏፏቴዎችና መብራቶች ያሉ፣ የካፒቶል ጎብኚዎች ማዕከል ሲገነባ እነዚህ መስህቦች ቀድሞ ወደነበራቸው ይዘት እንዲመለሱ ተደርጓል።

በካፒቶል ዙሪያ ገብ የፕሬዚደንቶች በዓለ ሲመቶች፣ የነጻነት በዓል ኮንሰርቶችና ከሦስት ሚሊዮን ሰዎች በላይ የሚሳተፉባቸው ዓመታዊ ጉብኝቶችን አስተናግደዋል። ይህን ታሪካዊ መልከአምድራዊ አቀማመጥ በመጎብኘት እንዲደሰቱ እንጋብዝዎታለን።



## በጉብኝትዎ ወቅት ማየት ያለብዎት



▲ የሊንከን ጠረጴዛ፣ የማሳቹሴትስ ሂስቶሪካል ሶሳይቲ

**ልዩ ጉብኝቶች፣ ንግግሮችና የቤተሰብ ፕሮግራሞች፡-** ይህ ወር በካፒቶል የጎብኚዎች ማዕከልን ይመልከቱ ወይም የካፒቶል የጎብኚዎችን ማዕከል ሠራተኞች ስለጉብኝት የጊዜ ሰሌዳ ይጠይቁ።

**የፕሬዚደንት አብርሃም ሊንከን ሁለተኛ በዓለ ሲመት ጠረጴዛ -** ጠረጴዛው የተሰራው የካፒቶል ጉልላት መስሪያ እንዲሆን ከቀረበው ብረት በተረፈው ነበር። (የትዕይንት አዳራሽ)

**በብርሃን አስተላላፊ ጣሪያው በኩል የጉልላቱ እይታ -** ከጎብኚዎች ማዕከል የታችኛው ወይም የላይኛው ደርብ ሆነው ወደ ላይ ብቻ ይመልከቱ!

**የነጻነት ሃውልት ፕላስተር ናሙና** - በካፒቶል ጉልላት ላይ የሚገኘውን፣ በነሃስ የተሰራውን የነጻነት ሃውልት ቅርጽ ለማውጫ አገልግሏል (ኢማኒሲፔሽን አዳራሽ)

**የሃውልቶች ስብስብ** - ከብሔራዊ የሃውልቶች አዳራሽ 100 ሃውልቶች መካከል 24 የሚሆኑት በመላው የካፒቶል የጎብኚዎች ማዕከል ይገኛሉ፤ ከእነርሱ መካከል 14 የሚሆኑት ሃውልቶች በኢማኒሲፔሽን አዳራሽ የሚገኙት ናቸው (የሃውልቶቹን ማብራሪያዎች በዚህ ፅሁፍ የሚቀጥሉት ገጾች ላይ ይመልከቱ)

**የሕዝብ እንደራሴዎችና የሴኔት ጋለሪዎች** - የጎብኚዎች ማዕከል የላይኛው ደርብ መግቢያ - የይለፍ ፈቃዶችን ከመጡበት ግዛት ሴኔተሮች ወይም የሕዝብ እንደራሴዎች ያግኙ።



**የባሪያ ጉልበት መዘከሪያ ምልክት** - ባሪያ የጉልበት ሠራተኞች በካፒቶል ግንባታ ላደረጉት አስተዋጽዖ ዕውቅና የመስጠት ሚና ያለው በድንጋይ የተሰራ ምልክት። (ኢማኒሲፔሽን አዳራሽ) ▶

**የካፒቶል ጉልላት ናሙና** - በሁሉም የኪነ ሕንጻ ዝርዝር ጉዳይ ትክክለኛ የሆነ ሊነካ የሚችል፣ የዋናው ጉልላት 1/20ኛ መጠን ያለው ናሙና። (የትዕይንት አዳራሽ)

**መዶሻ** - ፕሬዚደንት ጆርጅ ዋሽንግተን በ1793 የካፒቶል መሠረት ድንጋይ ባስቀመጡበት ሥነ ሥርዓት የተጠቀሙበት መዶሻ (የትዕይንት አዳራሽ)

**የሬሳ ሳጥን ማስቀመጫ፡-** በቀብር ስንብት ሥነ ሥርዓት ወቅት የፕሬዚደንቶችና ሌሎች ታዋቂ ዜጎች የሬሳ ሳጥን ማስቀመጫ (የትዕይንት አዳራሽ)

# U.S. CAPITOL
## የጐብኝት ማዕከል

**ነፃ ዋይ-ፋይ ለማግኘት**
**CVC-Guest ን ይጫኑ**

### መግለጫ

- የመረጃ ዴስኮች/ የጐብኝት የይለፍ ፈቃዶች
- ተሽከርካሪ ደረጃ
- አሳንሰር
- መጸዳጃ ቤቶች*

ጎብኚዎች በላይኛው ደርብ ከሚገኘው የጎብኚዎች መግቢያ በስተ ሰሜን በኩል ካለው የካፖርት ማቆያ ጣቢያ ወይም ከካፒቶል የጎብኚዎች ማዕከል ሠራተኞች በነጻ የሚሽከረከር ወንበር ጠይቀው ማግኘት ይችላሉ። ሁሉም መጸዳጃ ቤቶች ለሁሉም ጎብኝዎች ተደራሽ ናቸዉ።

* በሁሉም መጸዳጃ ቤቶች ለቤተሰብ የሚሆን መጸዳጃ ቤት ይገኛል።

## የላይኛው ደርብ




## የታችኛው ደርብ




## የስጦታ ዕቃ መደብሮች



**የስጦታ ዕቃ መደብሮች (የላይኛው ደርብ)፡-** የካፒቶልን ስዕሎችና የኪነ ሕንጻ ሃብቶች የሚያንጸባርቁ ልዩ ዕቃዎች፣ አስደሳችና አስተማሪ ስጦታዎች፣ መጽሐፍት፣ ጌጣ ጌጦችና አስደሳች እንደ ደንበኞች ፍላጎት የተነደፉ ምርቶችንና እጅግ ምርጥ የሆኑ የጉብኝት ማስታወሻዎችን ያገኛሉ።

9 a.m. – 4:30 p.m.፣ ከሰኞ እስከ ቅዳሜ



## የምግብ አገልግሎት

**የካፒቶል ካፌ (የታችኛው ደርብ)፡-** ትኩስ ሾርባ፣ ሰላጣ፣ ልዩ ምግቦች፣ ፒዛ፣ ሳንድዊቾች፣ ጣፋጭ ምግቦችና መጠጦች አሜሪካን የታደለችውን የተትረፈረፈ በረከት በአይነትም ሆነ በብዛት ያሳያሉ።

8:30 a.m. – 4 p.m.፣ ከሰኞ እስከ ቅዳሜ በካፒቶል የጎብኚዎች ማዕከል የሚገኙ ሃውልቶች

# በካፒቶል የጎብኚዎች ማዕከል የሚገኙ ሃውልቶች

በካፒቶል የብሔራዊ ሃውልቶች አዳራሽ በእያንዳንዱ ግዛት የተበረከቱ ሃውልቶችን ይዟል። እያንዳንዱ ግዛት ታዋቂ ግለሰቦችን ለመዘከር በሕግ አውጪዎቻቸው የተመረጡ ሁለት ሃውልቶችን ያቀርባል። በካፒቶል የጎብኚዎች ማዕከል ለዕይታ የቀረቡት 25ቱ ሃውልቶች (24 ከብሔራዊ የሃውልቶች አዳራሽ ስብስብ) የአገሪቱን ብዝሃነትንና በዜጎች የተበረከቱ አስተዋጽዖዎችን ያመላክታሉ።

ከ[visitthecapitol.gov/apps](visitthecapitol.gov/apps) የግዛት ሃውልቶችን የሚመለከት መረጃ ዳውንሎድ ያድርጉ።

ከሰዓሊው ስም በኋላ ያለው ዓመት ሃውልቱ በስብስቡ የተካተተበትን ዓመት ያሳያል።



**ፊሎ ፋርንስወርዝ** (1906–1971) ዩታ፣ ነሃስ፣ በጄምስ አቫቲ፣ 1990፤ የፈጠራው ሥራ ባለቤት። በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በነበረ ጊዜ በአዕምሮው የሳለውን የኤሌክትሮኒክ ቴሌቪዥን ሲስተም በመሥራቱ "የቴሌቪዥን አባት" ተብሎ ይጠራል። የቀድሞዎቹ ቴሌቪዥኖች በእርሱ የፈጠራ ባለቤትነት ከተመዘገቡ ፈጠራዎች መካከል 100ዎቹን ይጠቀማሉ። ኢንፍሬርድ የማታ ብርሃን፣ ኤሌክትሮን ማይክሮስኮፕ፣ አዲስ የተወለዱ ህፃናት ማሞቂያ፣ የጨጓራ ውስጥ ማሳያ፣ የአስትሮኖሚ ቴሌስኮፕና ራዳር ለማጎልበት ጥቅም ላይ ከዋሉ የፈጠራ ሥራዎች መካከል 160 ያህሉ በእርሱ ባለቤትነት የተመዘገቡ ናቸው። በ1920ዎቹ የፈጠረውን የኤሌክትሮኒክ ካሜራ ቱቦ ይዞ ይታያል።



**ፖፔይ** (1630? - ከ1692 በፊት) ኒው ሜክሲኮ፣ እምነበረድ፣ በክሊፍ ፍራጉዋ፣ 2005። ፑዌብሎ የኃይማኖትና መንፈሳዊ መሪ። በሳን ሁዋን ቡዌብሎ፣ አሁን ኒው ሜክሲኮ ተብሎ የሚጠራ ግዛት ተወለደ። በ1680 በስፔን ላይ የተደረገውን የፑዌብሎ አመጽ ያደራጀ ሰው ሲሆን፣ ይህ አመጽ የፑዌብሎ ባሕል ተጠብቆ እንዲቆይና የአሜሪካን ደቡባዊ ምዕራብ ክፍል ታሪክ በመቅረጹ ሂደት አስተዋጽዖ አድርጓል። የአመጹን ጊዜ ለማስተባበር ያገለግል የነበረውን የድብ ምስልና የተቆጣጠረ ገመድ ይዟል፤ ሃውልቱ የፑዌብሎ ባሕል ምልክት የሆነውን ማሰሮ አካቷል።



**ጂያኔት ራንኪን** (1880–1973) ሞንታና፣ ነሃስ፣ በቴሪ ሚንማውግ፣ 1985። ማኅበራዊ ሠራተኛ፣ ሌክቸረርና ከ1917-1919 እና ከ1941-1943 በሕዝብ እንደራሴነት ያገለገለች። የመጀመሪያዋ ሴት የኮንግረስ አባል። ስመ ጥር የሰላምና የሴቶች መብቶች አስተባባሪ። አሜሪካ ወደ 1ኛውና 2ኛው የዓለም ጦርነት እንዳትገባ ድምጽ የሰጠች። በ1941 በጃፓን ላይ የታወጀውን ጦርነት "ሴት እንደመሆኔ ወደ ጦርነት መሄድ አልችልም... ሌላውንም ወደ ጦርነት ለመላክ ፈቃደኛ አይደለሁም" በማለት የተቃወመች ብቸኛዋ የኮንግረስ አባል።



**ማሪያ ሳንፎርድ** (1836–1920) ሚኒሶታ፣ ነሃስ በኤቨሊን ሬይሞንድ፣ 1958። መምህርትና የሴቶች መብቶች ግንባር ቀደም ተከራካሪ። የሴቶችን የመምረጥ መብትና የአፍርካን አሜሪካዊያንን የትምህርት እድል የደገፈች፤ በጎልማሶች ትምህርትና የወላጆች - መምህራን ጣምራ ድርጅቶች ጽንሰ ሃሳብ ፈር ቀዳጅ። ከኮኔክቲከት ኖርማል ትምህርት ቤት ተመርቃለች። በስዋርትሞር ኮሌጅ የታሪክ መምህርት ነበረች። በሚኒሶታ ዩኒቨርሲቲ ደግሞ ለ20 ዓመታት ታስተምር ነበር። የኮሌጅ መምህርት ለመሆን ከበቁ የመጀመሪያዎቹ ሴቶች መካከል አንዷ ናት።



**ጆሴፍ ዋርድ** (1838–1889) ሳውዝ ዳኮታ፣ እምነበረድ በብሩኖ ቤግሄ፣ 1963። ሚሲዮናዊና መምህር። ሳውዝ ዳኮታ ራሱን የቻለ ግዛት እንዲሆን የተካሄደው እንቅስቃሴ መሪ። በዳኮታ ግዛት ዋና ከተማ ያንክተን ቅስናውን ያገኘ። ያንክተን አካዳሚን የከፈተና ለያንክተን ኮሌጅ መመስረት አስተዋጽዖ ያበረከተ። የግዛት ሕገ መንግሥት አርቃቂና የግዛቲቱ መፈክር አመንጪና ለግዛቲቱ ዓርማ ፍቺ የሰጠ ሰው ነው።



**ዊሊያም ኤድጋር ቦራህ** (1865–1940) አይዳሆ፣ ነሃስ በብራያንት ቤከር፣ 1947። ጠበቃ፣ ከ1907-1940 የዩኤስ ሴኔተር። የትምህርትና ሠራተኛ ጉዳይ ኮሚቴ ሊቀመንበር በነበረበት ወቅት የሠራተኛ ጉዳይ ዲፓርትመንትንና የሕጻናትን ቢሮ ማቋቋሚያ ሕግ እንዲወጣ ድጋፍ አድርጓል። የተደነቀ የመናገር ችሎታ የነበረውና "የአይዳሆ አንበሳ" ተብሎ ይጠራ የነበር።



**ጆን "ጃክ" ስዊገርት፣ ጁኒየር** (1931–1982) ኮሎራዶ፣ ነሃስ በጆርጅና ማርክ ሉንደን፣ 1997። ፓይለትና ጠፈርተኛ። በኮሪያ የጦር አውሮፕላን አብራሪና የሙከራ ፓይለት። የአክስጅን መያዣው ከተቀደደ በኋላ ተልዕኮው የተቋረጠው በ1970 በብሔራዊ ኤሮኖቲክስና ስፔስ አስተዳደር (ናሳ) አፖሎ 13 የጨረቃ ተልዕኮ ሦስት ተሳታፊዎች መካከል አንዱ ነበር። አባላቱ ከሞላ ጎደል ስድስት ቀናት በሕዋ አሳልፈዋል። የሕዝብ እንደራሴዎች ምክር ቤት የሳይንስና ቴክኖሎጂ ኮሚቴ ሥራ አስፈጻሚ ዳይሬክተር። በ1982 የሕዝብ እንደራሴዎች ምክር ቤት አባል ሆኖ ተመረጠ ነገር ግን ቦታውን ከመያዙ ከአንድ ሣምንት በፊት ከዚህ ዓለም በሞት ተለየ።



**ቺፍ ዋሻኪ** (1800?–1900) ዋዮሚንግ፣ ነሃስ በዴቭ ማክግሬይ፣ 2000። ጦረኛና የሾሾኒ ጎሳ አፈ ቀላጤ። የፈረንሳይኛ፣ የእንግሊዝኛና የበርካታ ሌሎች የኔቲቭ አሜሪካ ቋንቋዎች ብቁ ተናጋሪ። ብዙዎችን የሾሾኒ ንዑሳን ጎሳዎች ወደ አንድነት አምጥቷል። ከዩኤስ የጦር ኃይል ጋር በመደራደር ከ3 ሚሊዮን ኤከር  በላይ ስፋት ያለው መሬት የሾሾኒ መሬት ሆኖ እንዲጠበቅ አድርጓል። በተሟላ የዩኤስ ወታደራዊ የቀብር ሥነ ሥርዓት የቀብር ሥነ ሥርዓቱ ተፈጽሟል። አልባሳቱ በጥሩ ሁኔታ በህብረ ቀለማት ደምቀዋል።



**ኢዩሴቢዮ ፍራንሲስኮ ኪኖ** (1645–1711) አሪዞና፣ ነሃስ በሱዛን ሲልቨርክሩይስ፣ 1965። ሚሲዮናዊ፣ አገር አሳሽና ካርቶግራፈር። በጣሊያን የተወለደ የጄስዩት ቄስ። ወደ ሜክሲኮና ታችኛው ካፈሊፎርኒያ አሰሳ አድርጓል፤ በደቡብ አሪዞና ከሚገኙ ፒማ ኢንዲያንስ ጋር ሰርቷል። በካሊፎርኒያና አሪዞና የሚሲዮን ማዕከሎችን፣ የከብቶች ማርቢያና መንገዶችን ሰርቷል። አስትሮሌብ በመባል የሚታወቅ በከዋክብት ላይ ተመስርቶ ርቀት ለመለካት የሚያስችል መሣሪያ ይዞ ይታያል።



**ሳራ ዊነሙካ** (1844–1891) ኔቫዳ፣ ነሃስ በቤንጃሚን ቪክተር፣ 2005። ተርጓሚ፣ መምህርትና ጸሐፊ። የትውልድ ምንጯ ከነበረው የፔዩት ሕዝብና በዩኤስ የጦር ኃይል መካከል ድርድር አካሂዳለች። ለኔቲቭ አሜሪካዊያን ዜጎች ትምህርት ቤት ከፍታ በሕዝቡ የትውልድ ቋንቋና በእንግሊዝኛ ታስተምር ነበር። ላይፍ አማንግ ዘ ፓዩትስ:- ዜር ሮንግስ ኤንድ ክሌምስ የተሰኘው ግለ ታሪኳ የመጀመሪያው በኔቲቭ አሜሪካ ሴት የተጻፈ መጽሐፍ ነው። ሼልፍላወር ይዛ ትታያለች፤ ስሟ በፔዩት ቋንቋ ሼልፍላወር ማለት ነው።




**ንጉሥ ካሜሃሜሃ 1ኛ** (1758 ?–1819) ሃዋይ፣ ነሃስና ወርቅ፣ በ1879 የቶማስ ጎውልድ ተሰርቶ የነበረው ሃውልት ቅጂ፣ 1969። ተዋጊና ንጉሥ። ሁሉንም ሰዎች የሚኖሩባቸውን የሃዋይ ደሴቶች በራሱ አገዛዝ ስር አዋህዷል። ንግድን አበረታቷል፣ ሃዋይን ለሌላው ዓለም ክፍት አድርጓል። ሌላው መጠሪያው ስሙ ታላቁ ካሜሃሜሃ ነው። የሃዋይ ንጉሣዊ ልብስ፣ ቆብና በሃዋይ ማሞ ወፍ ላባ የተሰራ ካባ ደርቦ ይታያል።



ማዘር ጆሴፍ (1823–1902) ዋሽንግተን፣ ነሃስ በፌሊክስ ደ ዌልደን፣ 1980። ሚሲዮናዊትና አርክቴክት። በሞንትሬይል፣ ካናዳ አቅራቢያ ስትወለድ ኤስተር ፓሪሶ በሚል ስም ትጠራ ነበር። በ20 ዓመት ዕድሜዋ የካቶሊክ መነኩሲት ሆነች። ሚሲዮናዊያንን፣ ከዚያ በኋላ የዋሽንግተን ግዛት ተብሎ የተሰየመውን አገር ጨምሮ ወደ ፓስፊክ ሰሜን ምዕራብ ግዛቶች መርታለች። 11 ሆስፒታሎችን፣ ሰባት አካዳሚዎችን፣ አምስት የኔቲቭ አሜሪካን ነዋሪዎችን ትምህርት ቤቶችና ሁለት እናት አባት የሞቱባቸው ሕጻናት ማሳደጊያ ህንፃዎችን የነደፈች፣ የግንባታ ስራቸውን የተከታተለችና ለግንባታው ገንዘብ ያሰባሰበች። በማቆሚያው ላይ የሚታዩት የንድፍ ማውጫ መሣሪያዎችና ያሰራቻቸው አንዳንድ ሕንጻዎች ምስሎች ናቸው።



ሳሳካዌአ (1788 ?–1812) ኖርዝ ዳኮታ፣ ነሐስ፣ ሃውልት በ1910 ተሰርቶ የነበረው ሃውልት ቅጂ ነው፣ ሊዮናርድ ክሩኔል፣ 2003። ተርጓሚና አስጎብኚ። በ1805 በአገር አሳሾቹ በሜሪዌዘር ልዊስና ዊሊያም ክላርክ ከሚመራው ቡድን ጋር ጨቅላ ልጇን ይዛ ወደ ሰሜን ምዕራብ በተካሄደው አሰሳ እገዛ አድርጋለች። የእርሷ መኖር ለአካባቢው ጎሳዎች አሰሳው ሰላማዊ ነው የሚል መረዳት እንዲኖራቸው አድርጓል። እንደ ተጓዥ፣ ተርጓሚ፣ ዲፕሎማት፣ ሚስትና እናት ክብር ተሰጥቷታል። ሂዳስታ የተባለው የእርሷ ጎሳ ሳሳካዌአ ወይም “ወፏ ሴት” የሚል ስያሜ ተሰጥቷታል።



ሄለን ኬለር (1880–1968) አላባማ፣ ነሃስ በኤድዋርድ ሃላቭካ፣ 2009። ጸሐፊ፣ መምህርትና ለአካል ጉዳተኞች መብትና የሌሎች ማኅበራዊ ጉዳዮች ተከራካሪ። በሕጻንነት ዘመኗ ባጋጠማት ሕመም ምክንያት ዓይነ ስውርና መስማት የተሳናት ነበረች። የምልክት ቋንቋና ንግግር እንዲሁም ብሬል ተማረች። የመጀመሪያዋ ዓይነ ስውርና መስማት የተሳናት የኮሌጅ ተመራቂ ናት። “ለዓለም የአሜሪካ የበጎ ፈቃድ አምባሳደር” በመባል ትታወቃለች። በቱስኩምቢያ፣ አላባማ በሚገኘው ቤቷ በ7 ዓመቷ በውሃ መሳቢያ አጠገብ ሆና ትታያለች፤ ለመጀመሪያ ጊዜ “ውሃ” የሚለውን ቃል በምልክት ቋንቋ ያወቀችውና ከሰው ጋር መግባባትን የተማረችው በዚያ ነበር።



## የነጻነት ሃውልት



በካፒቶል ጉልላት ላይ የሚገኘው በነሃስ የተሰራ የነጻነት ሃውልት ዋናው የፕላስተር ናሙና ወደ ቀድሞው ይዘቱ እንዲመለስ ተደርጎ ለጎብኚዎች ዋናውን ሃውልት ወክሎ በቅርብ የሚታይ በካፒቶል የጎብኚዎች ማዕከል የኢማኒሲፒሽን አዳራሽ ዋናው የትኩረት መስህብ ሆኗል። ናሙናው የ19½ ጫማ ቁመትና በግምት የ13,000 ፓውንድ ክብደት ያለው ነው።

በ1857 ቶማስ ክራውፎርድ የተባለ በሮም ከተማ ይሰራ የነበረ አሜሪካዊ የቅርጻ ቅርጽ ባለሙያ የነጻነት ሃውልትን የፕላስተር ናሙና አጠናቀቀ። ከክራውፎርድ ሞት በኋላ ሌላ ክላርክ ሚልስ የተባለ አሜሪካዊ የቅርጻ ቅርጽ ባለሙያ በዋሽንግተን ዲሲ በሚገኘው የብረት ማቅለጫ ተቋሙ እንዲሰራው ተደረገ። ሞዴሉን ያቀናጀው ሠራተኛ ምክንያታዊ ባልሆነ መልኩ ተጨማሪ ክፍያ ካልተሰጠው በቀር የሀውልቱን ናሙና በየክፍሉ እንደማይለያየው በመናገሩ ምክንያት ፊሊፕ ሬይድ የተባለ የክላርክ ሚልስ ባሪያ የነበር ሞልዱ ወደ ብረት ማቅለጫው ተወስዶ መስራት እንዲቻል ክፍሎቹ እንዴት መለያየት እንደሚችሉ ወሰነ።

በማቅለጫው፣ ሬይድ በሞልዶቹ ውስጥ እሳቱ እየነደደ እንዲቀጥል የማድረግ ኃላፊነት ተሰጥቶት ነበር፣ ከሌሎች ባሮች የጉልበት ሠራተኞች ጋር በመሆን የፕላስተሩ ሞዴል ክፍሎች በነሃስ እንዲሰራ አደረገ። ፊሊፕ ሬይድ የነሃስ ሃውልቱ በ1862 ወደ ካፒቶል ከመወሰዱ ከጥቂት ጊዜ በፊት ከባርነት ነጻ ወጣ፤ ሃውልቱ በጉልላቱ ላይ በዲሴምበር 2 ቀን 1863 በተቀመጠ ጊዜ ነጻ ሰው ነበር።

◀ የነጻነት ሃውልት ናሙና በኢማንሲፔሽን አዳራሽ በግራ በኩል ወደ ትዕይት አዳራሽ መግቢያው ላይ ግርማ ሞገስ ባለው ሁኔታ ቆሞ ይታያል።

## በካፒቶል የጎብኚዎች ማዕከል የላይኛው ደርብ የሚገኙ ሃውልቶች

የሚከተሉት አራት ሃውልቶች በላይኛው ደርብ በምስራቅ በኩል በሚገኘው የእንግዳ ማስተናገጃ የኢማንሲፔሽንን አዳራሽ ከላይ ሆነው እንደሚያዩ ሆነው ቆመዋል።



**ጁሊየስ ስቴርሊንግ ሞርቶን** (1832–1902) ኔብራስካ፣ ነሃስ በሩዱልፍ ኤቫንስ፣ 1937። አርሲ.ደር፣ ሕግ አውጪና የካቢኔ አባል። በእርሱ የልደት ቀን ኤፕሪል 22 የሚከበረውን የአርበር ቀን መሥራች። ነብራስካ ግዛት ከመሆኗ በፊት የይገባኛል ጥያቄ አቅርቦ ነበር። የግዛቱ ሕግ አውጪ አባልና ጸሐፊ ሆኖ አገልግሏል። በፕሬዚደንት ክሊቭላንድ የአስተዳደር ዘመን የግብርና ሚኒስትር ሆኖ አገልግሏል። በበርካታ ጥራዝ የተጻፈውን በስዕል የተደገፈ የኔብራስካን ታሪክ በዝርዝር የሚያስረዳ መጽሐፍ በአርታዒነት ማዘጋጀት ጀመረ። በሃውልቱ ስር የአርበር ቀን ምልክቶች የሆኑ የዛፍ ግንጣይ፣ ሊጋ ችግኝ፣ የተከል መግረዝና አካፋ ይታያሉ።



**ኤድዋርድ ዳግላስ ዋይት** (1845–1921) ሉዚያና፣ ነሃስ በአርተር ሞርጋን፣ 1955። ጠበቃ፣ የግዛት ሕግ አውጪ፣ የዩኤስ ሴኔተር 1891-1894፣ ከ1894-1921 የዩኤስ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኛ፣ ከ1910-1921 የዩኤስ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰብሳቢ ዳኛ ሆኖ አገልግሏል። በ16 ዓመቱ የኮንፌዴሬት ጦር አባል ሆነ፣ ሆኖም ግን የጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኛ በነበረበት ወቅት አፍርካን አሜሪካን የመምረጥ መብት ሊኖራቸው ይገባል የሚለውን ሀሳብ ደግፏል። ለጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኝነት የተሾመው በፕሬዚደንት ክሊቭላንድ ነበር።



**ኧርነስት ግሩኤኒንግ** (1886–1974) አላስካ፣ ነሃስ በጆርጅ አንቶኒሰን፣ 1977። ጋዜጠኛ፣ የአላስካ ግዛት ገገር ገና ከ1959-1969 የዩኤስ ሴኔተር ነበር። ከሕክምና ትምህርት ቤት የተመረቀ ቢሆንም በቦስተንና ኒው ዮርክ ሪፖርተር፣ ኤዲተርና ማኔጂንግ ኤዲተር ሆኖ ሰርቷል። የአላስካ ኢንተርናሽናል ሃይዌይ ኮሚሽንን እንዲመራ ተሹሞ ሰርቷል። ከ1939 ጀምሮ ጡረታ እስከወጣበት 1953 ድረስ የግዛቱ ገገር ሆኖ አገልግሏል። ከሁለቱ የአላስካ የመጀመሪያ ሴኔተሮች መካከል አንዱ ነበር። "አላስካ ግዛት እንድትሆን ያስቻለ አባት" ተብሎ ይታወቃል።



**ጀምስ ክላርክ** (1854–1916) አርካንሳስ፣ እምነበረድ በፖምፒዮ ኮፒኒ፣ 1921። ከ1903 -1916 ጠበቃ፣ የግዛት ሕግ አውጪ አባል፣ ዋና ዓቃቤ ሕግና የግዛቱ ገገር እንዲሁም የዩኤስ ሴኔተር። ለሁለት ጊዜያት ያህል የሴኔቱ ጊዜያዊ ፕሬዚደንት ሆኖ ተመርጧል። የፓናማን ካናል ፕሮጀክትና የፊሊፒንን ነጻ መውጣት ደግፏል። የሴኔት የንግድ ኮሚቴ አባል እንደመሆኑ የሠራተኞች ኃላፊነትና ካሣ ሕግን ለማጽደቅ ድጋፍ አድርጓል።

### የካፒቶልን ሥነ ጥበብ ስለማክበር

በጉብኝትዎ ወቅት የካፒቶልን ሃውልቶችና ሌሎች የሥነ ጥበብ ሥራዎች ጠብቆ ለማቆየት እንዲቻል ድጋፍ ያድርጉ። በመመልከት ብቻ ደስ ይበልዎ ነገር ግን በእጅዎ አይንኩ - በእያንዳንዱ የመንካት ጊዜ የተወሰነ ጉዳት ይደርሳል።

## ከካፒቶል የጎብኚዎች ማዕከል ውጭ ያሉ ሃውልቶች

ከዚህ በማስከተል የተጠቀሱት በሃውልቶች አዳራሽ ስብስብ ውስጥ የሚካተቱ ስድስት ሃውልቶች በጎብኚዎች ማዕከል ለሕዝብ ክፍት ከሆኑ ቦታዎች ውጪ ያሉ ናቸው። ከእነዚህ ሃውልቶች መካከል ማንኛውንም ለማየት ከፈለጉ፣ እባክዎን ከጎብኚዎች ረዳት ጋር ይነጋገሩ።

**ጆን ክሌይተን** (1796–1856) ዴላዌር
**ጀምስ ጆርጅ** (1826–1897) ሚሲሲፒ
**ዌድ ሃምፕተን** (1818–1902) ሳውዝ ካሮላይና
**ኤፍሬም ማክዶዌል** (1771–1830) ከንተኪ
**ዶ/ር ጆን ማክሎግሊን** (1784–1857) ኦሪገን
**ጀነራል ኪርቢይ ስሚዝ** (1824–1893) ፍሎሪዳ

## የሰብዓዊ መብት መሪዎችን ማክበር



**ፍሬድሪክ ዳግላስ** (1818–1895)በታልቦት ካውንቲ ሜሪላንድ በባርነት ቀንበር ሥር ተወለደ። በአገሪቱ እጅግ ከፍተኛ ተጽዕኖ ማድረስ የቻለ የሲቪልና ሰብዓዊ መብቶች ተሟጋች ነበር። በ1838 ከባርነት ካመለጠ በኋላ መኖሪያውን በኒው ቤድፎርድ፣ ማሳቹሴትስ በማድረግ የባርያ አሳዳሪ ሥርዓትን በማፍረስ ሂደት ውስጥ ተሳታፊ ሆነ። ለ25 ዓመታት በኖረበት በሮቸስተር ኒው ዮርክ ሦስት ግለታሪኮችን ጽፏል፤ እንዲሁም የመሪነት ሥፍራ የነበረውን የአፍሪካን አሜሪካዊያንን ጋዜጣ ያሳትም ነበር። በእርስ በእርስ ጦርነቱ ጊዜ ዳግላስ ለአዲሶቹ የአፍሪካን አሜሪካዊያን ክፍለ ጦሮች ወታደሮች መልምሏል። በ1872 ወደ ዋሽንግተን ዲሲ ተዘዋወረ ከዚያም በተደጋጋሚ ጊዜያት የመንግሥት ሥልጣን ይዞ ከቆየ በኋላ በ1895 በዋሽንግተን ዲሲ ከዚህ ዓለም በሞት ተለየ። ዳግላስ ለአፍሪካን አሜሪካዊያንና ለሴቶች የመምረጥ መብት፣ ነጻ ለወጡ ሰዎች እኩልነት፣ ከፍርድ ውጪ ግድያን ለማስቀረት ህግ እንዲወጣ ያላሰለሰ ጥረት አድርጓል። በኮንግረስ በወጣ ሕግ፣ በስቲቨን ዊትዝማንን የፈጠራ ውጤት የሆነውና በዲስትሪክት አፍ ኮሎምቢያ የተበረከተው የፍሬድሪክ ዳግላስ ሃውልት በጁን 19 ቀን 2013 በኢማንሲፔሽን አዳራሽ እንዲቆም ተደርጓል።



በትውልድ ስሟ ኢዛቤላ ባውምፍሪ በ1797 በባርነት ቀንበር ሥር ተወለደች፤ በኋላ **ሶጆርነር ትሩዝ** በሚል ሥም የተጠራችሁ ይህች ሴት ገና የዘጠኝ ዓመት ልጅ ሳለች በጨረታ ለባርነት ተሸጠች። የ30 ዓመት ዕድሜ ሲሞላት ኢዛቤላ በአምስት የተለያዩ ባሪያ አሳዳሪዎች ባለቤትነት ሥር ትኖር ነበር። በኃይማኖቷ ምክንያት ኢዛቤላ ስሟን ሶጆርነር ትሩዝ በሚል ቀየረች፤ በዚህም ምክንያት ባርነትን ስለመገርሰስና ስለሴቶች መብቶች ታስተምር ነበር። በአርቲስ ሌን የተሰራው የሶጆርነር ትሩዝ ከወገብ በላይ ሃውልት በዩኤስ ካፒቶል አንዲትን አፍሪካን አሜሪካዊት ሴት ለመዘከር የመጀመሪያው ነው። ለመጀመሪያ ጊዜ በኢማንሲፔሽን አዳራሽ የታየው በኤፕሪል 2009 ነበር።



**ራውል ዋለንበርግ** የስዊድን ዲፕሎማት ሲሆን፣ በ2ኛው ዓለም ጦርነት በቡዳፔስት በነበረው የአገሩ ሌጋሲዮን አማካኝነት በአስር ሺዎች የሚቆጠሩ በወራሪው የናዚ ጦርና በሃንጋሪያዊያን ተባባሪዎቻቸው በአደጋ ላይ የወደቁ አይሁዳዊያንን ለማዳን ችሏል። በሚሪ ማርገሊን የተሰራው የዋለንበርግ ከወገብ በላይ ሃውልት በ1995 በኮንግረስ ተቀባይነት አገኘ።

## የካፒቶል ጉብኝት አስቀድሞ ወረፋ ማስያዝና የይለፍ ፈቃዶች

**በካፒቶል የጎብኚዎች ማዕከል ሲደርሱ ጉብኝቱን ለማድረግ አስቀድመው ወረፋ ይዘው ከነበረና** ወረፋ መያዣ ማረጋገጫዎትን ወይም የማረጋገጫ ቁጥርዎን ከያዙ እባክዎ የካፒቶል ጉብኝት የይለፍ ፈቃድ ለማግኘት እንዲችሉ በታችኛው ደርብ በቀኝ (ሰሜን) በኩል ወደሚገኘው የመረጃ ዴስክ ይሂዱና ፈቃዱን ይቀበሉ።

በካፒቶል የጎብኚዎች ማዕከል ሲደርሱ፣ ከዚህ ቀደም ለጉብኝት ወረፋ ይዘው ካልሆነ ፣ በታችኛው ደርብ በግራ በኩል (ደቡብ) በሚገኘው የመረጃ ዴስክ **"Visitors without Reservations"** ተብሎ ወደሚታወቀው ስፍራ ይሂዱ።

**በካፒቶል ጉብኝት ወቅት ምን መጠበቅ እንዳለብዎ** - በአስጎብኚ አማካኝነት የሚካሄደው የካፒቶል ጉብኝት የሚጀምረው 13 ደቂቃ በሚፈጅ የማስተዋወቂያ ፊልም ሲሆን የፊልሙም ርዕስ "Out of Many, One." የተሰኘ ነው። ይህን ፊልም በዓለም ዓቀፍ ቋንቋዎች ለማዳመጥ ማዳመጫዎችን ከመረጃ ዴስክ ጠይቆ ማግኘት ይቻላል። ይህ መሣሪያ በፊልሙ የሚነገሩትን ቃላቶች ይተረጉማል። ራሱን የካፒቶልን ጉብኝት ግን አይተረጉምም።

**ዓለም ዓቀፍ የካፒቶል ጉብኝት መከታተያ መረጃ ሰጪ ፅሁፎች** ከጉብኝቱ ዋና ዋና ነጥቦችን የያዘ ከእንግሊዝኛ ይልቅ በሌሎች ቋንቋዎች በጎብኚዎች ማዕከል በታችኛው ደርብ ከሚገኙት የመረጃ ዴስኮችና ከአስጎብኚዎች ማግኘት ይቻላል። ሌሎቹ ቋንቋዎች አማርኛ፣ ዓረቢኛ፣ ቻይንኛ፣ ፈረንሳይኛ፣ ጀርመንኛ፣ ሂንዲኛ፣ ጣሊያንኛ፣ ጃፓንኛ፣ ኮሪያንኛ፣ ፖርቹጋልኛ፣ ሩሲያ ቋንቋ፣ ስፓንሽኛና ቬትናምኛ ናቸው።

**የትዕይንት አዳራሽ ማዳመጫ መሣሪያዎች፡**- ጎብኚዎች ከመረጃ ዴስኮች ለትዕይንት አዳራሽ የድምፅ ጉብኝት የሚሆን የዓለም ዓቀፍ ቋንቋ ማዳመጫ መሣሪያዎች ለማግኘት ጥያቄ ማቅረብ ይችላሉ።

**እባክዎን ያስታውሱ፡**- የዩኤስ ካፒቶል ጉብኝቶች ያለ እቅድ እንዳይካሄዱ ወይም እንዲቋረጡ ሊያደርግ ይችላል። ይህ ሲሆን ማስታወቂያዎች በ**www.visitthecapitol.gov** ና በማኅበራዊ ሚዲያ ይወጣሉ።

የዩኤስ ካፒቶልን ስለጎበኙ ምስጋና እናቀርባለን።

እርስዎ የሚሰጡን ግብረመልስ ለእኛ አስፈላጊ ነው። ያጋጠመዎትን ልምድ በ**comments@visitthecapitol.gov** ለሌሎች ያካፍሉ።

U.S. CAPITOL

www.visitthecapitol.gov
Twitter @visitthecapitol
www.visitthecapitol.gov/apps

CVC 18-122